# ★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞ ቅጽ 44 ቁ 3** **የካቲት/መጋቢት 2011**


## ሥር ነቀል የሥርዓት ለውጥ በሽግግር ሂደት

የካቲት የድላችን አርማ ነው፤ የካቲት ለአገራቸው ሲሉ በግፍ የተጨፈጨፉ ኢትዮጵያዊያን ሰማዕታት መታሰቢያ ነው። የካቲትን ስንዘከር የአገራቸውን ክብር በጠላት ከርሰመቃብር ላይ ለማረጋገጥ በቀድሞ ቤተ መንግሥት በዛሬው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ የአገርና የወገንን ክብር ላለማስደፈር በግራዚያኒ ላይ ቦምብ በመወርወር ክቡር መስዋዕት የሆኑት አብርሃም ደቦጭ፣ ሞገስ አስገዶምንና ሌሎች እልፍ አእላፍ ጀግኖቻችን የሚታወሱበት ታሪካዊ ወር ነው። ፋሽስቶች በአዲስ አበባ ነዋሪ በነበሩ ኢትዮጵያውያን ላይ ከፍተኛ ጭፍጨፋ ያካሄዱበት፤ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውን ንጹህ ደም እንደጎርፍ በከተማዋ አደባባይ የፈሰሰበት የሀዘን ወር ነው።

ባንጻሩ የየካቲት 1966 አብዮት ክስተትንም በዚህ ወር አብረን እናስታውሳለን። የየካቲት አብዮት ከፈነዳ ድፍን 45ዓመታት ያስቆጠረ ሲሆን የጀግኖች ወገኖቻችንን የአርበኝነት ፈለግ በመከተል መሬት ለአራሹ ይሁን፤ ዳቦ ለተራበው ይሰጥ፤ የሃይማኖትና የፆታ እኩልነት ይከበር የሚለውን መሠረታዊ የትግል መፈክር ያስተጋቡትና ውድ ህይወታቸውን ጭምር መሰዋዕት በማደረግ የተዋደቁትን የዚያን ትውልድ ምሁራንና ታጋዮች በአንክሮ እናስታውሳለን። እነዚህ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች ብዙኀኑ ሕዝብ ከብዝበዛ ተላቆ የመሬቱ ባለቤት እንዲሆን ሲጠይቁ በወቅቱ በአገሪቱ ላይ በገሀድ ይታይ የነበረውን የብሔረሰብ ጭቆናና የእኩልነት መጥፋት ደግሞ በዝምታ ሳያልፉ በእኩልነት ላይ ለተመሰረተ አንድነት ተጋድለዋል። የሕዝብ አንድነት በዴሞክራሲና በሕዝብ ሙብት መረጋገጥ ላይ ተመሥርቶ ለሀገር አንድነትና ብልጽግና መገንቢያ ይሁን በማለት ተሟግተዋል።

የየካቲት 1966-ኡ የለውጥ እንቀሰቃሴ ጥሪ ድብብቆሽ ጠፍቶ ሐቁ ተገልጦ ይውጣ ፤ ጭቆና አለና እናስውግደው ፤ ተባብረን እንነሳ፤ እኩልነትን እናረጋግጥ፤ ሀገራችን ከድህነትና ከኋላቀርነት ተላቃ እንደሌሎች የበለጸጉ አገሮች በእደገትና በልማት ጎዳና ትራመድ በሚል ቆራጥ መንፈስ የተደረገ እንጂ የአፍ አርበኞች እንደሚሉት በጎጠኞችና በባእዳን የተጠነሰሰ ሴራ አልነበረም። ሐቁ የዚያን ትውልድ ራዕይ የሚያመላክት ብሩህ ተስፋን ለሀገሩ ከሰነቀ ትውልድ የታለመ በጎ ህልም ነበር። ዛሬም ነው።

የየካቲቱ እንቅስቃሴ፤ ላባደሮች፥ ተማሪዎች፤ አብዮታዊ ምሁራን፣ መምህራን፣ የመንግሥትና የቢሮ ሠራተኞች፣ ወታደሮችና ባለሌላ ማዕረጎች፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች፣ አርሶአደሮች የተሳተፉበት ለአንድነት፤

ለእኩልነትና ለፍትህ የተደረገ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ነበር። የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎች በወቅቱ ከፍተኛ እልቂት እያደረሰና በአፄው መንግሥት ተደብቆ የነበረውን ድርቅና ረሃብ ይፋ በማውጣትና የባለሥልጣኖቹንም እኩይ ተግባር በማጋለጥ ትልቅ ሚናን ተጫውተዋል። መምህራንና ተማሪዎች "ሴክተር ሪቪው" በመባል ይታወቅ የነበረውን አዲስ የትምህርት ፖሊሲም አጥብቀው በመቃወማቸው ለየካቲቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የማይናቅ አስተዋፆ አበርክትዋል።

የዚያ ትውልድ የተማረው ክፍል የኢትዮጵያን ሁኔታ እንዴት መለወጥ እንደሚቻል አምርሮና አጠንክሮ መጠየቅና መመርመር የጀመረ፤ የሀገሩን የሩቅና የቅርብ ሁኔታዎችን በመገምገም በአገራችን ይታይ የነበረውን ኋላቀር ሥርዓትና በዓለም ደረጃም የቅኝ ግዛትን መስፋፋት በመቃወም ለኢትዮጵያም ሆነ ለአፍሪካ የተሻለ ሥርዓት የሚመሰረትበትን በጎ ራዕይ ያነገበ ለውጥ ፈላጊ ትውልድ ነበር። ዛሬ በታሪክ በራዦችና ከሀዲዎች የሚዥጎደጎደው የሀሰት ክምር ይህን ሐቅ ሊሸፍን ከቶም የሚችል አይደለም ።

የየካቲት ወር፤ በሀገራችን ውስጥ ትምህርትን፣ ሕክምናን፣ ሥራን ለሁሉም ዜጋ ለማዳረስ የብዙሃኑን መብትና ጥቅም በእኩልነት ለማስከበር፤ የብሔር ጭቆናን ለማስወገድ ፤ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የአገር አንድነትን ለማስረጽ ፤ ማኅበራዊ ፍትህን ለማስገኘት ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ቴክኖሎጂካዊ እድገትን ለማምጣት ትልቅ ዓላማን አንግቦና ብሩህ ተስፋን ይዞ የተሰባሰበ፤ ከራሱ ጥቅም ይልቅ ሀገሩንና ህዝቡን ያስቀደመ ለመሠረታዊ ለውጥ የቆመ ያ ትውልድን የምንዘክርበት ታሪካዊ ወር ነው። ያ ጀግና ትውልድ ስለ ለውጥ ማውሳት ብቻ ሳይሆን ለውጡን እውን ለማድረግ ታግሏል፤ ሕይወቱን ገብሯል። የትግል ታሪክ ሀሁ ያልገባቸው ወጥ አለቀ ብለው ቢይላዝኑም የሞሶሊኒን ጦር ሲጋተር ከሚሊዮን ያላነሰ ሕዝባችን ሕይወት አልባ መሆኑን መገንዘብ የተሳናቸው ፍጡሮች ናቸው። መስዋዕትነትን የማይጠይቅ ትግል ሊኖር እንደማይችል የቅርቡ ጸረ ወያኔ ትግላችን ራሱ በሚገባ ያስረገጠ ሲሆን አሁንም ለሀገር አንድነት ለመሰዋት ዝግጁ ሆኖ መገኘት የሀገር ወዳዱ ሁሁ ግዳጅ ነው። የካቲት ያስተማረንም ይህ ነው ።

የካቲትን ለማስተወስ ይህን ካልን ዘንድ አገራችን እየተጓዘችበት ያለውን አሳሳቢ እና አሳፈሪ ሁኔታ መመርመርና በመፍትሔው ላይ መምከር አግባብነት ይኖረዋል። በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እየታየ ያለው ምስቅልቅል ፤ ሥርዓት አልበኝነት፥ ግርግርና መፈናቀል፥ የዘረፋና ግድያ መበራከት፥ የሕዝቡ ደህንነት መናጋትና የሰላም መጥፋት ከየት የመጣ ነው፤ ብሎ ለጠየቀ መልሱ እምብዛም አዳጋች ሊሆን አይችልም። ሀገራችን ኢትዮጵያን ለ27 ዓመታት በላይ ሲዘርፍና ሕዝቧንም ጨቁኖ ሲገዛ የነበረ ዘረኛና በዝባዥ የሆነው የወያኔ ወንጀለኛ ቡድን በሥልጣን ለመቆየት ሕዝብን በዘርና በቋንቋ ሲከፋፍልና ሲያጣላ የቆየ በመሆኑ ነው። ችግሩና ምስቅልቅሉ አድማሱን አስፍቶ ሊቀጥል የቻለውም ከተለያዩ ብሔርና ብሔረሰቦች የተመለመሉ ቅጥረኞች ከዚሁ ቡድን ጋር በጥቅም ተሳስረው ፤ እጅና ጓንት ሁነው አብረው እየሰሩ ስለነበረም ጭምር ነው። ስለሆነም ለዚህ ሁሉ ችግር አሁንም ተጠያቂው ይኸው ከፋፋይ ቡድንና በውጭና በውስጥ ያሉ ተባባሪዎቹ ለመሆናቸው፥ ዋቢ መጥራት አስፈላጊ አይሆንም።

የችግሩ ሁሉ ፈጣሪና መነሻ የሆነው የወያኔ ቡድን፥ በጥገና ለውጥ ተቀባብቶ መልሶ የመፍትኄው አባወራ አካል ሆኖ መቅረቡ በራሱ የሚያመጣው መዘዝ ብዙ ነው። ከላይ የነበሩትን፥ ለጊዜው ዞር አድርጎና ከበታች ያለውን መዋቅር እንደነበረ ትቶ ለውጥ መሻት ፥ ከእባብ እንቁላል እርግብን መጠበቅ ያህል ይሆናል። ለሥርዓቱ በደሎች ዋና ዋናዎቹ ተጠያቂዎች፥

በአመራር ደረጃ ተቀምጠው በፈላጭ ቆራጭነት የወያኔን ተልዕኮ ሲያስፈፅሙ የነበሩ መሪዎች፤ የበላዮቻቸውን መመሪያ በማስፈፀምና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሕዝብ ላይ በጭካኔ ግፍ ሲሰሩ የነበሩ አሁንም በየቦታው ባሉት መዋቅሮች ውስጥ ተሰግስገው ይገኛሉ።

ዛሬም በየአቅጣጫው የሚታየውና እየሆነ ያለው ሁሉ ፥ በቅርበት ቢመረመርና ቢገመገም ፥ በአንድ በኩል፥ በወያኔው መዋቅር ውስጥ የተሰገሰጉ ቡድኖች፥ የነበረውን መዋቅር በመጠቀም ቀድሞ ወደ ነበሩበት የሥልጣን ቦታ ለመመለስ እየጣሩ መሆናቸው በግልፅ የሚታይ ነው። ሌሎች ደግሞ ይህንን ክፍተት በመጠቀም ፅንፈኛ አስተሳሰባቸውን በሕዝብ ላይ ለመጫን የጥላቻና የሸብር አጀንዳቸውን ከነዚሁ ፀረ ህዝብ ኃይሎች ጋር በማጣመርም ሆነ በተናጠል የሕዝብ ወገን መስለው መርዛቸውን እየረጩ ይገኛሉ። የለውጥ ተብዬው እንቅስቃሴ እንግዲህ፤ እነዚህን ሁሉ አቅፎ ጥገናዊ ለውጥ ለማምጣት ሲውተረተር ይታያል። በአሁኑ ወቅት ሽግግር እያደረግን ነው የሚለው ክፍል በሕዝብ ያልተመረጠ አካል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ባለፈው አገራዊ ምርጫ ከፍተኛ የማጭበርበር ተግባር ፈጽሞ መቶ በመቶ አሸነፌያለሁ በማለት በሥልጣን የተሰየመ አካል መሆኑ መታወቅ አለበት። ይህንን አይን ያወጣ ማጭበርበር ትክክል አይደለም የሚባልበት የፍትህ ሥርዓት የሌለበት፤ ቀማኛውም ዳኛውም እራሱ የሆነበት ሁኔታ አሁንም እንዳለ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ያሉትን ወያኔዎችና የዛሬ ለውጥ አምጪ በሉን ባዮች ሥልጣን ላይ ያስቀመጣቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን አሜሪካና አረቦች ለመሆናቸው ደግሞ በቂ መረጃ ሲቀርብ ቆይቷል። ይህ በመሆኑም የተከሰተው ሁኔታ በሀገሪቱና በሕዝብ ላይ ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ይገኛል። ያላለፉት 10 ወራት እንቅስቃሴ እንዳሳየው ፤ የችግሩ ፈጣሪና ምክንያት የሆነው ኃይል የመፍትሄው አካል ነኝ በሚል አማጭና አዋላጅ ጨርሶ ሊሆን እንደማይችል በበቂ ያስመሰከረበት ሁኔታ ጎልቶ ታይቷል።

ይህ አሳሳቢ ሁኔታ ጊዜ አግኝቶ ከቀጠለ ከፍተኛ ሀገራዊና ማኅበራዊ ቀውስ ሊከተል እንደሚችል መገመት አያስቸግርም። ለዚህም ኢሕአፓ ደግሞ ደጋግሞ ለማሳወቅ እንደሞከረው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብና ሐቀኛ ዜጎች መሠረታዊና ሥር ነቀል ለውጥ ሊያስገኝ የሚችለውን የሽግግር ሂደት በእጃቸው ሊያስገቡት ይገባል ይላል። ሰላማዊና አስተማማኝ የሽግግር ሂደት እንዴት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል የሚለው ወሳኝ ጥያቄ መልስ ማግኘት አለበት። ከዚህ በፊት የኢሕአፓ ልሳን ዴሞክራሲያ ስለ ሽግግር ምንነት እንዲህ ብሎም ነበር።

> "ዴሞክራሲያዊ ሽግግር፣ መጭው ትውልድ፣ እስከ ዝንተዐለሙ፤ በማንኛውም ጊዜ ከሚነሳ አምባገነን ወታደራዊ ኃይል ሆነ አስመሳይ ቡድን መብቱን ለሚጠብቅበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት የሚጥል፤ መንገዱን የሚያስተካክልና የሚጠርግ ክስተት ነው። ስለሆነም የሽግግሩ ዐብይ ዓላማ ፤ የአገሪቱ የወደፊት ዕድል በአንድ ነፍጥ በታጠቀ የፖለቲካ ቡድን እጅ በድጋሚ እንዳይወድቅ ለማድረግና ወሳኙና አድራጊፈጣሪው ሕዝብ ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።" (ዴሞ ቅፅ 43 ቁ 4 2010)

ይሁን እንጅ አሁን በሥልጣን ላይ ባለው ቡድን ይሁንታ ወይም በጎ አመለካከት አለን ብለው ራሳቸውን በሚከቡና ከዛው ሥርዓት በወጡ ግለሰቦች መልካም ምኞት ፥ ሁነኛና አስተማማኝ ሽግግር ሊኖር እንደማይችል ከወዲሁ ልናረጋግጥላቸው እንወዳለን። ሽግግር በቀድሞው ሥርዓት መዋቅርና በባለሟሎቹ ሊተገበር የሚችል ክስተት አይደለም። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መሠረት ለመጣል የሚካሄድ ዴሞክራሲያዊ ሂደት እንጂ። ይህም ሂደት፥ ሕዝብን ከመንደርና ከቀበሌ ጀምሮ

እስከ ከፍተኛው የአስተዳደር መዋቅር ድረስ ፥ ሙሉ ለሙሉ የሚያሳትፍ ሲሆን አካሄዱም የሕዝባዊ እንቅስቃሴ ውጤት መሆን አለበት። የሀገር ሰላምና ደህንነት ተጠብቆ ፥ መካሄድ ያለበት ሐቀኛ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ነው።

ይህ የሽግግር ሂደት፥ በአስተማማኝ መሠረት ላይ እንዲቆም፥ ስለአስፈላጊነቱና ስለሂደቱ ምንነት እንዲሁም እንዴት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ውይይቱ በሰፊው መጀመር ይገባዋል። በዚህ የውይይት ሂደት ሕዝብ በሚመቻቸው መድረክ፤ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና የማኅበረሰቡ ክፍሎች በየደረጃው መሳተፍ አለባቸው። በየክፍለ አስተዳደሩ ያሉትና የነበሩት የሥርዓቱ መዋቅሮች ሕዝቡ በሚወክላቸውና በሚያምናቸው ተመራጮቹ መተካት አለባቸው። እነዚህ ጊዜያዊ የአስተዳደርና የሰላም አስጠባቂ ተግባራት በሕዝቡ ቁጥጥር ሥር መዋል አለባቸው። ሕዝብንና አካባቢውን የማረጋጋት እንዲሁም የእርቅና የመግባባት ሂደቱን ሊያውኩ የሚችሉትን ሁሉ ጠንቅቆ መለየትና በሕግ አግባብ ጥግ እንዲይዙ ማድረግ፥ ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ሁሉ በጥንቃቄ መዝጋትና ማስወገድ አስፈላጊ ይሆናል።

ከሕዝብ ዐይንና ጆሮ የሚሰወር ስለሌለ ፥ እስካሁን ድረስ ሕዝብንና ሀገርን ሲያውኩ የነበሩትንና ዛሬ ደግሞ ኮት ቀይረው፥ የሌለ ለውጥ አራማጅ ሆነው፥ ሽር ጉድ የሚሉትን ሁሉ ፥ ልቅም አድርጎ ማውጣትና እስካሁን ላደረሱት ጉዳት ሁሉ በተገቢው መንገድ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ፤ የሽግግሩ ሂደት አንድ ዋነኛ ተግባር ሊሆን ይገባል። ይህ ጉዳይ በከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲካሄድና ከጅምላ ፍርድ የጸዳ እንዲሆን ሐቀኛ የፍርድ ሂደትን የተከተለ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ማድረጉ ተገቢ ነው። በየአካባቢው ከሚገኙ ፥ ከሕዝብ አብራክ የወጡ ፥ አመኔታውን ያተረፉ፥ የጸጥታ አስከባሪ ኃይሎችን፥ ፖሊሶችና ፌደራሎችንም ጭምር፥ ማካተትና መጠቀም - ሕዝብ ለነማን አመኔታ እንዳለው ጠንቅቆ ያውቃልና !። በተመሳሳይም፥ በፍትህ ሥርዓቱም ፥ ዳኞችና አቃቢ ዳኞችን ለይቶ በሕዝብ አመኔታ የሚጣልባቸውን አደራጅቶ የፍትህ ሥርዓቱን ሕዝባዊ ይዘትና ቅርጽ በመስጠት መልሶ ማቋቋም አስፈላጊ ይሆናል።

በኢሕአፓ እምነት፥ የኢትዮጵያ ህዝብ ረጅም ዘመናትን ባስቆጠረው አብሮ የመኖር ታሪኩ በርካታ ማኅበራዊና የግንኙነት ችግሮቹን የሚፈታበት ባህልና ዘዴዎችን ያዳበረ ህዝብ ነው። የተለያዩ የእምነት ተከታዮች፥ ነገዶችና ብሄረሰቦች፥ ኩታ ገጠም አካባቢዎችና ነዋሪዎቻቸው ፥ ተከባብረውና በሰላም ግጭቶችንና ውዝግቦቻቸውን የሚፈቱባቸው መንገዶችና ሥርዓቶችን ያበጁና በጋራ ያዳበሩ ለመሆናቸው፥ ምሳሌ ወይም መረጃ ማቅረብ አስፈላጊ አይሆንም። ለሺዎች ዓመታት አብሮ የመኖር፥ በጋራ የውጭ ወራሪዎችን በአንድነት የመመከት ሚስጢራቸውም ይኼው እሴታቸው ነው። እስላም ክርስቲያን፥ የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪዎች፥ ያለ ምንም ችግር ተጋብተውና ተዋልደው የሚኖሩባት ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም። በትክክል መጠቀም ከተቻለ፥ ይህ ሀገራዊ እሴትና ጠንካራ ባህል፤ የሽግግር ሂደቱን የተሳካ ሊያደርገው የሚችል መሠረት ነው ብሎ ኢሕአፓ ያምናል።

በዚሁ፥ ዝንተ ዓለም ባስቆጠረ ታሪካዊ ሂደት ፥ ይህቺን ውብ ሀገር ሊነጥቁን የቋመጡ ፥ በተለያየ ጊዜ የመጡብን ጠላቶችና ወራሪዎች፥ ሕዝቧን እንደ ድርና ማግ የያዘውን አንድነት መበጣጠስ ዋና ዓላማቸው አድርገው ሞክረዋል። መቼውንም አልተሳካላቸውም። አሁን በኛ ዘመን ደግሞ የገጠመን የተለየ ባይሆንም፥ እንደዘመኑ ስልታቸውን አዘምነውና ቀያይረው፥ እሾህን በሾህ እንዲሉ፥ በገዛ "ዜጎቻችን"፥ ባረጃ ባፈጀ መንገድ ሊፈታተኑን፣ አዳዲስ ባንዳዎችን ካሰማሩብን ከሦስት ዓሥርተ ዓመታት በላይ አስቆጥረዋል። የሃይማኖትና የጎሳ ወይም የብሔረሰብ የእርስ በርስ ግጭት በመጫርና ጥቃቅን ልዩነቶችን

አጉልቶ አንድ የሚያደርጉንን እሴቶቻችንን በመካድና በማንኳሰስ ፤ እኛነታችንን ከእኛችን ፈልቅቀው ሊቀሙን ሲውተረተሩ ይታያሉ። በዚህ የሽግግር ወቅት ፥ የተሻለ ሕዝብን ያሳተፈ ሽግግር እንዳይኖር ፥ ከሚገረግሩን ኃይሎች ጋር በአንድ ላይ ናቸው። ሕዝብ ደስ እንዲለውና በሰላም እንዲኖር አይወዱም፥ ከግልና ከቡድን ፍላጎታቸው ውጪ የታወሩ ናቸው። የወያኔው ሥርዓት ውላጆች ናቸውና ፤ ይህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ከሥር መሠረቱ ተነቅሎ እንዲወገድ አይሹም። ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር እውን እንዳይሆን እንቅፋት ናቸው።

የቅርብ ጎረቤቶቻችንና የሩቅ ባዕዳንም፥ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴያችንን፥ ከራሳቸው ሀገራዊ ጥቅም አንፃር ብቻ የሚከታተሉ በመሆናቸው፥ ይህን የሽግግር ሂደት ለነሱም በሚበጅ መልኩ ለመቃኘት የማይሞክሩት አይኖርም። ዛሬ፥ ትርጉም የሌለው የእርስ በርስ ፍጅት በየአቅጣጫው ለማፋፋም እየተሯሯጡ ያሉ ቡድኖችና ግለሰቦች ሁሉ ፥ በወያኔ ብቻ ሳይሆን በነግብፅና በሌሎችም፥ ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች፥ ረጅም እጆች የሚዘወሩና የተሰማሩም ሊሆኑ እንደሚችሉ መጠርጠር ሲያንስ ነው። በቅርብም ጎረቤት ሱዳን፥ እንደዛሬ በራሷ የውስጥ ችግርም ተወጥራ እንኳን ፥ በምዕራቡ የሀገራችን ድንበር ያሉንን ለም መሬቶች ይዛ ለመቆየትና በጉልበት የራሷ ለማድረግ እየጣረች ትገኛለች። ስለሆነም፥ በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲና ለአንድነት የሚደረገውን ትግል፥ እንደወትሮዋ ከወያኔው ሥርዓት ጎን በመቆም አጋሯን ለማዳንና ፍላጎቷን ለመጠበቅ ትዋደቃለች። በቀይ ባሕር አካባቢ የነኤሚሬትና ሳውዲዎቹ ዱለታ የኛን ስጋት የሚጨምር እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም።

ከዚህ ሁሉ ችግር፥ ሀገራችንን መንጥቆ ለማውጣት ዋነኛው መንገድ ብለን የምናምነው ፥ የለውጡን ሂደት ባለቤቱ፥ ህዝቡና ሀቀኛ ልጆቹ በእጃቸው ሲያስገቡና ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ሂደቱን ሲቆጣጠሩ ብቻ ነው። ኢሕአፓ/ኢሕአሠ ሲንቀሳቀስ በነበረባቸው ጎንደርና ጎጃም ክፍሎች ፥ ህዝቡ በየቀበሌው የራሱን አስተዳደር መስርቶ፥ የፍርድ ሸንጎዎችንም ሰይሞ ፥ የአካባቢ ጥበቃውንም አቋቁሞ ፥ በሰላም መኖር የቻለበት ተሞክሮ አሁንም ፥ ለዚህ የሽግግር ሂደት ሊታይ የሚገባው ይመስለናል። ከዚህም ደረጃ በደረጃ ሊያድግና ለጊዚያዊ የሽግግር ሂደቱ መሰረት ሊሆን እንደሚችል እናምናለን። ለዚህም በሕዝባችን ሙሉ እምነት አለን። ስለሆነም፥ ሁሉም ሀገር ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይላት፥ ድርጅቶችና ግለሰቦችም፥ ለሀገሪቱና ሕዝቧ አንድነትና ሉዓላዊነት ፥ ራዕይ ያላቸው ሁሉ ፥ በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ፥ ጥቃቅን ልዩነቶችን ወደ ጎን አድርገው ፥ ኢትዮጵያን ለማዳንና ለመታደግ ሰልፋቸውን ያሳምሩ ዘንድ፥ ኢሕአፓ አሁንም ደጋግሞ ጥሪውን ያቀርባል።

ሽግግርም ሆነ የመጨረሻው ድል የህዝብ ነው !